የኢፌዲሪ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት

FDRE TECHNICAL & VOCATIONAL TRAINING INSTITUTE

# የመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ፖሊሲ ሪፎርም ማስተግበሪያ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ

**ሰኔ 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**ማውጫ**

1. መግቢያ ........................................1
2. ጥቅል ዓላማ ......................................2
3. ዝርዝር ዓላማ .....................................2
3.1. ግንዛቤን ማሳደግ ..................................2
3.2. አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ እሳቤዎችን በአግባቡ መምራት ..........2
3.3. ግልጽነት መፍጠር ..................................2
3.4. ስኬቶቹን ማስተዋወቅ ................................2
4. ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ..................................3
4.1. የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮዎች ............................3
4.2 ተቋማዊ የሁኔታዎች ትንተና ............................4
4.3. ሀገራዊ የልማት ትልሞች .............................5
4.4. የቴክኖሎጂ እድገትና ዲጂታላይዜሽን ......................5
4.5. ተለዋዋጭ ዓለማዊ ሁኔታዎች ...........................6
4.6. ተቋማትን ማጠናከር ለሀገረ መንግስት ግንባታው ያለው አስተዋፅኦ ......6
5. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች ያላቸው ወሳኝ ሚና..........7
6. ባለድርሻ አካላት .....................................7
6.1. ውስጣዊ ባለድርሻ አካላት ............................7
6.2. ውጫዊ ባለድርሻ አካላት .............................7
7. ቁልፍ መልዕክቶች እና የኮሙኒኬሽን ቻናል ......................8
7.1. ቁልፍ መልዕክቶች ..................................8
7.2. የምንጠቀማቸው የኮሙኒኬሽን ቻናል .......................11
8. የአደጋ ጊዜ ግንኙነት ................................12
9. የሚጠበቁ ውጤቶች ...................................12
10. የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ስልቶች፤ ..................13
11. የክትትልና የግምገማ ስርዓት፤ ..........................13
12. ማጠቃለያ .........................................14
13. የድርጊት መርሀ ግብር .................................20

# 1. መግቢያ

በዘመናዊው ዓለም የመንግስት አገልግሎት እና አስተዳደርን ማሻሻል ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ነው። የአሰራር ሂደቶችን በማቀላጠፍ እና አላስፈላጊ ቢሮክራሲያዊ መሰናክሎችን በመቀነስ የህዝብ አገልግሎቶች በፍጥነት እና በብቃት እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል። ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመከተል የህዝቦችን ፍላጎት በበለጠ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግም ይጠበቃል፡፡ ይህ ወጪዎችን ለመቆጠብ የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን ያሳድጋል፡፡ የግልጽነትና ታማኝነት ጥያቄዎች በበዙበት በዚህ ወቅት መንግስት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበትን አሰራር መዘርጋት መቻሉ በዜጎች ላይ እምነት ለመፍጠር ያግዛል። ይህ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም እንደ ሀገር ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተጠያቂነት ያለው እና የዜጎችን ሁለንተናዊ ደህንነት የሚያጎለብት አገልግሎት መስጠት የሚችል የሲቪል ሰርቪስ ስርዓት ለመገንባት ያስችላል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አዲሱን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ለመተግበር ከተመረጡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መካከል አንዱ መሆኑን ተከትሎ በስሩ የሚገኘው የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት እንደ ተጠሪ ተቋምነቱ ሪፎርሙን ተግባራዊ ለማድረግ በኢንስቲትዩቱ በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ለመላ ሰራተኞች በሪፎርሙ መሠረታዊ ይዘት፣ ዓላማዎች እና የአፈጻፀም አቅጣጫዎች ዙሪያ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስልጠና በመስጠት የቅድመ ትግበራ ዝግጅት ስራውን የጀመረ ሲሆን ሪፎርሙ የሚፈልጋቸውን ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን ፈጥሮና ተገቢ አቅጣጫ አስቀምጦ ወደ ስራ እንዲገቡ አድርጓል፡፡

በኢንስቲትዩቱ የተፈጠሩት አደረጃጀቶች ከመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም አበይት ጉዳዮች ጋር በተናበበ መልኩ ሲሆን እያንዳንዱ አደረጃጀት ተግባሩን የሚፈጽምበትን ዕቅድ በማውጣት ወደ ተግባር እንቅስቃሴ መግባት ችሏል፡፡ ዕቅዶቹ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ላይ ያሉ ውስንነቶችን በመለየት በኢንስቲትዩቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማረጋገጥ፣ ቅልጥፍናን ለማላቅ፣ ውጤታማነት ለማሻሻል እና ሙያዊ ብቃትን መሰረት ያደረገ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት ታሳቢ ተደርገው የተዘጋጁ ሲሆን እነሱን መነሻ በማድረግ ይህንን የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ እቅድ በማዘጋጀት ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

ይህ በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ተግባራዊ የሚደረገው የመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ግብ ምላሽ ሰጪ፣ ዘመናዊ እና ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቪስ ለመፍጠር ያለመ በመሆኑ በኢንስቲትዩቱ በየደረጃው የሚገኙ ሠራተኞችን ባለቤትነት፣ የጋራ ጥረት እና ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ሠራተኞችና አመራሮች እንዲሁም ባለድርሻ እና አስፈፃሚ አካላት ተግባራዊ ስለሚደረገው የመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ሪፎርም ስራ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ለስኬቱ የበኩላቸውን እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መነሻነት በየደረጃው የሚሰራው የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ ለሪፎርሙ ስኬት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ሥራው የሚመራበትን ግልጽ ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የተዘጋጀው ስትራቴጂ ተግባራዊ ከሚደረገው የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲ ማሻሻያ አኳያ ነባራዊ ሁኔታውን በመዳሰስ ጥቅልና ዝርዝር ዓላማ፣ ግብ፣ ባለድርሻዎችን፣ ቁልፍ መልዕክቶች፣ የኮሙኒኬሽን ቻናልና ስልቶች እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ስርዓትን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ በስትራቴጂው ግልጽነት ለሪፎርሙ ስኬት መሰረት

እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ ይህ ሪፎርም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውና ሪፎርሙ ተጽዕኖ የሚያሳድርባቸው አካላት ወቅታዊ መረጃዎች በተከታታይ የሚያገኙበትና ግንዛቤያቸውን ማሳደግ የሚቻልበት ስልትም ተመላክቷል፡፡

## 2. ጥቅል ዓላማ

በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ለሚተገበረው ሀገራዊ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ውጤታማነት መላ ሠራተኛው፣ ባለድርሻ እና አስፈፃሚ አካላት በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ለስኬቱ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

## 3. ዝርዝር ዓላማ

### 3.1. ግንዛቤን ማሳደግ

- ሪፎርሙን አስመልክቶ ለኢንስቲትዩቱ መምህራንና ሰራተኞች፤ ባለድርሻ እና አስፈፃሚ አካላት ግልጽ የሆነ መረዳት እንዲኖራቸው ማስቻል
- ሪፎርሙ የሚኖረውን ሁለንተናዊ ፋይዳ አስመልክቶ ለኢንስቲትዩቱ መምህራንና ሰራተኞች በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ለትግበራው ዝግጁ እንዲሆኑ ማስቻል

### 3.2. አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ እሳቤዎችን በአግባቡ መምራት

- ሪፎርሙን በተመለከተ በመምህራንና ሰራተኞች ዘንድ ሊፈጠሩ የሚችሉ የተጋነኑ ግምቶች እና የተዛቡ አስተሳሰቦችን እንዲሁም ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ጉዳዮችን በመለየት ምላሽ መስጠት፣
- መምህራንና ሰራተኞች በሪፎርሙ ትግበራ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን ስጋት በማስወገድ አመኔታ እንዲኖራቸው መስራት፣
- ሪፎርሙን ተከትሎ ሊኖር የሚችለውን የመምህራንና ሰራተኞች ምዘና፣ ማብቂያና ማትጊያ እንዲሁም ከምደባና ጥቅማ ጥቅም ጋር ተያያዥነት ያላቸው አሰራሮች ላይ በቂ መረጃ ተደራሽ ማድረግ፣
- በሪፎርም ትግበራ ወቅት መምህራንና ሰራተኞች  በተረጋጋ መንፈስ በመደበኛ ሥራቸው ላይ እንዲያተኩሩ ማስቻል፤

### 3.3. ግልጽነት መፍጠር

- የሪፎርም ትግበራ ሂደቱ የደረሰበትን ደረጃ በየወቅቱ ማሳወቅ፣
- መምህራንና ሰራተኞች አስፈላጊ መረጃ በቀላሉ የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

### 3.4. ስኬቶቹን ማስተዋወቅ

- በሪፎርም ትግበራ ሂደት በየደረጃው የተገኙ ውጤቶችን ማስተዋወቅ፤

- በሪፎርም ትግበራው የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት፤

## 4. ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ

የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የሚፈልጉትን ብቁ የሆነ አሰልጣኝና የተቋም አመራር ማፍራት፣ ተወዳዳሪ የሆኑ የኢንዱስትሪ ቴክኒሽያኖችን ለገበያ የማቅረብ፣ ዘርፉን በተለያዩ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር እንዲሁም በቴክኖሎጂና ኢንተርፕራይዝ ልማት መደገፍ ላይ ያተኮሩ ተልዕኮዎቹን በላቀ መልኩ ለመፈፀም የሚያስችል ልዩ ልዩ ሪፎርሞችን ቀርፆ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በስራና ክህሎት ሚኒስቴር ስር ከሚገኙ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲ ከሚተገበርባቸው ተጠሪ ተቋማት መካከል አንዱ በመሆኑ የጀመራቸውን የሪፎርም ሥራዎች የበለጠ ለማጎልበት እድል የሚሰጠው እንደሆነም ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህ የተጀመረው የመንግሰት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም በኢንስቲትዩቱ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ መምህራንና ሰራተኞች እንዲሁም አመራሩ የእኔ ነው እንዲቀበለውና ለተግባራዊነቱም የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ የተጠኑና አግባብነት ያላቸው የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ይህንን በሚፈለገው አግባብ ሥራ ላይ ለማዋል ያሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፈተሸና መቃኘት አስፈላጊ እንደመሆኑ በሪፎርም ሂደቱ የሚሰሩ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች መነሻ የሚያደርጓቸው ተቋማዊ፣ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ተዳሰዋል፡፡

### 4.1. የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮዎች

ሀገራዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ ዋነኛ ዓላማ የስራ ገበያውን መነሻ ያደረገ ጥራት ያለው ስልጠናን  ለሁሉም የኢኮኖሚ መዋቅሮች በየደረጃው ተደራሽ በማድረግ ድህነትን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ውስጥ የራሳቸውን አሻራ ማኖር የሚችሉ ብቁ፣ ተነሳሽና ስራ ፈጣሪ ዜጎችን ማፍራት ላይ ያለመ ነው፡፡

ይህን ሀገራዊ ተልዕኮ ለማሳካት የአንበሳውን ድርሻ በመያዝ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስኬታማነት ትልቅ አቅም በመሆን ጉልህ ድርሻውን እያበረከተ የሚገኘው የኢፌዲሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት የዘርፉን አሰልጣኞች፣ አመራሮችና የኢንዱስትሪ ቴክኒሺያኖችን ከማፍራት ባሻገር ችግር ፈቺና ለፖሊሲ ግብአት የሚሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሁም የቴክኖሎጂ ልማት ላይ በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የቆመለትን ግብ ለማሳካት ማለትም ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ውጤታማነት ጉልህ ድርሻ ያላቸውን አሰልጣኞችና የተቋማት አመራሮችን በመደበኛና በተከታታይ የስልጠና ፕሮግራም በማብቃት፣ በጥናትና ምርምር የዘርፉን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የሚያስችሉና ለፖሊሲ ግብአት የሚሆኑ ተከታታይ ጥናቶችን በማድረግ፣ ባደገ አስተሳሰብ ላይ ተመስርቶ በተለያየ መንገድ ማህበረሰብ ተኮር አገልግሎቶችን በመስጠት እንዲሁም በቴክኖሎጅና

ኢንተርፕራይዝ ልማት ላይ ተቋሙን የቴክኖሎጂ መፍለቂያ ማዕከል ለማድረግ ብሎም ሞዴል ኢንተርፕራይዝ በመፍጠር ለሌሎች ማሳያ የሆነ ተቋም ለመፍጠር በትኩረት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የዘርፉን አዳዲስ እሳቤዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተግበር እንደ ዋነኛ አቅም ሆኖ እያገለገለ ከመሆኑም ባሻገር ተልዕኮውን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግና ያስቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት በተቋም ደረጃ 11 ያህል የሪፎርም እሳቤዎችን ቀርጾና ተቋማዊ አደረጃጀትን ፈጥሮ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን በዚህም አበረታች ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን አዲሱን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳዳር ማሻሻያ ሪፎርም እሳቤዎች በተገቢ መንገድ በመተግበር ተልዕኮውን በተሻለ መንገድ መወጣት የሚችልበትን እድል መፍጠር ላይ በትኩረት ሊሰራ ይገባዋል፡፡ ለዚህ ስኬት የኮሙኒኬሽን ስራዎች የሚኖራቸው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

### 4.2 ተቋማዊ የሁኔታዎች ትንተና

የኢፌዲሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት የስራ ገበያውን ባማከለ ሁኔታ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትና አሰልጣኞችና አመራሮችን፣ የኢንዱስትሪ ቴክኒሺያኖችን ወቅቱ በሚፈልገው እውቀትና ክህሎት ለማብቃት፣ በጥናትና ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ረገድም የዘርፉንና የማህበረሰብን ችግሮች በሳይንሳዊ ጥናት ለመፍታት የሚያስችሉና ለፖሊሲ ግብአት የሚሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ኢንዲያከናውን በቴክኖሎጂና ኢንተርፕራይዝ ልማት በኩልም ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች የሚፈጠሩበት፣ የሚለሙበትና ኮሜርሻላይዝ የሚደረጉበት መደላድል እንዲፈጠር ለዚህም የመሪነት ሚናውን እንዲጫወት የሚጠበቅበት ሲሆን ይህንን ተልዕኮውን ለመወጣት ከ700 በላይ መምህራንና ሰራተኞችን አቅፎ እየሰራ የሚገኝ ትልቅ ተቋም ነው፡፡

ከተቋማዊ አደረጃጀት አንጻር ከዋናው ግቢ በተጨማሪ የቴክኖሎጂ ልማትና የብየዳ ልህቀት ማዕከል ያለው ሲሆን ማዕከሉ ቴክኖሎጂ ፍብረካና አቅም ግንባታ ስልጠና ላይ አተኩሮ ይሰራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተመረጡ 15 ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ላይ የሳተላይት በመክፈት በረጅም ጊዜ ፕሮግራም የአሰልጣኝ መምህራንን የአቅም ግንባታ ተግባር እያከናወነ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ያለውን ውስን ሀብት በመጠቀም ለዘርፉ ስኬታማነት እያበረከተ ያለው ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል አሁን እየታሰበ ካለው የሪፎርም ስራ ጋር የማይሄዱና መሻሻል ወይም እንደ አዲስ መዘጋጀት የሚኖርባቸው  የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች፣ መመሪያና ደንቦች መኖራቸው፣ የውስጥ አሰራር፣ ግንኙነትና የተግባቦት ባህል፣ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የሰው ሃይል ስምሪትና የአቅም ግንባታ ስራዎች፣ የሀብት አጠቃቀምና ተቋማዊ አደረጃጀትን መፈተሸ እንደሚገባ፣ አሰራርን ከማዘመን አንጻር የሚታዩ ክፍተቶችን ማረምም ወሳኝ መሆኑ የተቋሙ የሁኔታ ዳሰሳ ጥናት ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ከተለያዩ ሀገራት፣ ከትምህርት ተቋማት፣ ከግሉ ዘርፍ በተለይም ከኢንዱስትሪው ጋር ያለውን ግንኙነት እያጠናከረ መምጣቱ እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት እየተጀመሩ ያሉ የአጋርነት ስምምነቶች ኢንስቲትዩቱ ተልዕኮውን ለማሳካት እንዲችል ትልቅ አቅም የሚሆኑት በርካታ መልካም አጋጣሚዎች

እንዳሉት የሚያሳይ ሲሆን በትግበራ ሂደት ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ውጫዊ ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉም ታሳቢ ይደረጋል፡፡

የኢፌዲሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት አስቀድሞ በተቋሙ ውስጥ የጀመራቸው የሪፎርም እሳቤዎች መኖራቸውና ለዚህም ተግባራዊነት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችና የተቋሙ ሰራተኞችም በሪፎርም ስራ ውስጥ በንቃት እየተሳተፉ መሆናቸው አሁን በመንግስት ደረጃ የታሰበውን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ሪፎርም ለመተግበር እንደ አንድ ልምድ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎን ኢንስቲትዩቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሰው ሀይል አደረጃጀቱን በአዲስ መልክ እያደራጀ መሆኑ ለሪፎርም ትግበራው ምቹና ጥሩ ልምድ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡

በጥቅሉ ኢንስቲትዩቱ ተልዕኮውን በላቀ ደረጃ ለመፈጸምና እየታሰበ ያለውን ሪፎርም ለማሳካት እንዲችል ከተለመደው አሰራር ወጣ ብሎ ማየትን የሚጠይቀው ይሆናል፡፡ ለዚህም በዋናነት ከአሰራር፣ ከአደረጃጀት፣ ከተግባቦት አንጻር የሚስተዋሉ ችግሮችን በተገቢ መልኩ ለመቅረፍ የሚያስችል ስልት በመቀየስ መስራትን የሚጠይቅ ሲሆን በሰራተኛው ዘንድ አስፈላጊው መረዳትና የሀሳብ ስርጸት እንዲኖር በኮሙኒኬሽን ረገድ ሰፊ ስራ መስራትን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

## 4.3. ሀገራዊ የልማት ትልሞች

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ትልቅ የመልማት ተስፋን ሰንቃ ያለች ሀገር ስትሆን ያላት የሰው፣ የተፈጥሮና ልዩ ልዩ ሀብቶችን በሚገባ መጠቀም መቻል የልማት ውጥኗን እውን ለማድረግ አይነተኛ አማራጭ ነው፡፡ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር የሚደረገው ጥረት ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ከሚሰራው በርካታ ስራ ጎን ለጎን ለኢንዱስትሪው የጀርባ አጥንት ሆኖ የሚያገለግል በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ማዘጋጀትን ይፈልጋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና በሙያው ብቁ የሆነ፣ ተነሳሽነት ያለው፣ ከሁኔታዎች ጋር በቀላሉ የሚላመድና ለፈጠራ ዝግጁ የሆነ ዜጋን በማፍራት ለኢኮኖሚው እድገትና ለድህነት ቅነሳ ትግሉ ብሎም የሚታሰበውን የዘላቂ ልማት ግብ ለማሳካት ጉልህ ድርሻ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

ይህንን ግብ እውን ለማድረግ በየደረጃው የተለወጠ አስተሳሰብ፣ ዝግጁነትና የሚታይ ተግባር ይፈለጋል፡፡ ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የሚስተዋለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ይዞ የሚታሰበውን ለውጥ ማምጣት የሚቻል አይሆንም፡፡ ስለሆነም እንደ ተቋም የሲቪል ሰርቪሱን አቅም ማጠናከር፣ የሰራተኛውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ተወዳዳሪነቱን ማሳደግ እንዲሁም በስነ ምግባሩ የታነጸና የአገልጋይነት ስሜት የተላበሰ ማድረግ ወሳኝ ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንንም ተከታታይ በሆነና በተደራጀ የኮሙኒኬሽን ስራዎች በመደገፍ ዳር ማድረስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 4.4. የቴክኖሎጂ እድገትና ዲጂታላይዜሽን

ይህ ወቅት ዓለማችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በሚገኝ የቴክኖሎጂ ለውጥና እልህ አስጨራሽ ፉክክር ውስጥ የምትገኝበት ነው፡፡ በአዲስ መልክ ተፈብርከው የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች ሳይውል ሳያድር በላቀና በረቀቀ ቴክኖሎጂ ሲተኩ ማየትም የዓለማችን የዕለት ከዕለት ትዕይንት እየሆነ መጥቷል፡፡ ዲጂታላይዜሽንና ሰው ሰራሽ አስተውሎት የዓለማችንን ብሎም የህዝቦቿን አኗኗር ባልተለመደ ሁኔታ እየቀየሩት እንደሆነ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ ሁኔታዎች በፍጥነት ተለዋዋጭ በሆኑበት ዓለም ውስጥ ህልውናን አስጠብቆ ለመኖር የሚያስችል ብቃትና ተወዳዳሪነትን መላበስ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል የስልጠና ስርዓትን መዘርጋት የለውጥን ሥጋት ለመቆጣጠር ከሚያስችሉ ስልቶች መካከል ዋነኛ ሆኖ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል የዲጂታላይዜሽን እድገት ሰዎች ማንኛውንም አገልግሎት ፈጣን፣ ቀልጣፋና ቀላል በሆነ መልኩ የሚያገኙበትን ነባራዊ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በዚህ መልኩ የተፈጠረውን ፍላጎት ለማስተናገድ የሚያስችል ብቃትን መላበስ የተገልጋይን እርካታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁልፍ ጉዳይ መሆኑንም ልብ ማለት ያሻል፡፡

የኢፌዲሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ዲጂታላይዜሽንን ከማስፋፋት ረገድ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በቅርቡ የተገነባው የዲጂታል ስቱዲዮ መረጃን በአግባቡ ለማድረስ እድል የሚሰጥ ሲሆን በሌላ በኩል ስልጠናውን ለማዘመን በተቋሙ እየተፈጠሩ ያሉ አደረጃጀቶችና እየተሟሉ ያሉ ግብአቶች እንዲሁም የe-learning (Blended learning) የስልጠና አማራጮች መጀመራቸው ዲጂታላይዜሽንን ከማሳደግ አንጻር ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

ምንም እንኳን ኢንስቲትዩቱ ለዲጂታላይዜሽን የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ቢሆንም አጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥን ከማዘመንና ተቋማዊ ተልዕኮን ከፍ ወዳለ ደረጃ ከማድረስ አንጻር ሲቃኝ ሰፊ ስራ የሚጠይቀው ይሆናል፡፡

የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂው ዲጂታላይዜሽንን ጥሩ አማራጭ አድርጎ መጠቀም ላይ መስራትና የተለያዩ የዲጂታላይዜሽን ይዘቶችን በማበልጸግ ሪፎርሙን በተለያየ መንገድ ማስተዋወቅና በቂ ግንዛቤን መፍጠር የሚጠበቅበት ይሆናል፡፡

## 4.5. ተለዋዋጭ ዓለማዊ ሁኔታዎች

ዓለማችን እያስተናገደቻቸው ያለችውን ከባድና ፈታኝ ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ አንዳንድ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን አሁን ያለንበትን ጊዜ VUCA world (volatility, uncertainty, complexity and ambiguity) በማለት ይገልፁታል፡ ይህ በግርድፉ ሲተረጎም በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ የሚችል የታመቀ ችግር ያለበት፣ ለመገመት የሚያስቸግር፣ የተወሳሰበና አሻሚ ገፅታን የተላበሰ ጊዜ ላይ የምንገኝ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ አኳያ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናችንም ተለዋዋጭ በሆነው ሀገራዊና ዓለማዊ ሁኔታ ውስጥ ለሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችና ቀውሶች ምላሽ የመስጠት አቅም እንዲኖረው ማስቻል ወሳኝ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የሲቪል ሰርቪሱም ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በቀለቀሉ ሊላመድ የሚችል ተገቢውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ጥበብ እንዲላበስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የኮሙኒኬሽን ስራዎች ነባራዊውን ሁኔታ በአግባቡ በመዳሰስና በመረዳት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግንዛቤን የማሰጨበጥና ለለውጥ የማዘጋጀት ትልቅ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 4.6. ተቋማትን ማጠናከር ለሀገረ መንግስት ግንባታው ያለው አስተዋፅኦ

ኢትዮጵያ የብዙ ዘመናት የሀገረ መንግስት ግንባታ ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም ሂደቱ መላው ኢትዮጵውያንን ያላሳተፈ መሆኑ ብሎም በዘመናት እየተንከባለሉ የመጡና ምላሽ ያላገኙ የህዝብ ጥያቄዎች በመኖራቸው ሳቢያ የሀገረ መንግስት ግንባታው የተሟላና ያለቀለት ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ በመሆኑም የተረጋጋች፣ ሠላማዊና የበለፀገች አገርን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ያለፉት ዘመናት የቤት ሥራዎችን፣ የዛሬን ተጨባጭ ፍላጎትና የነገን መፃኢ ዕድል መሰረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ጠንካራ ሀገረ መንግስትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ጠንካራ ተቋማትን ዕውን ከማድረግ ይጀምራል፡፡ ተቋማት ግልጽ የሆነ ራዕይና ተልዕኮን አንግበው ተገቢውን አደረጃጀት ፈጥረውና የሰው ሀብታቸውን በተገቢ መንገድ አዘጋጅተው የሚጠበቅባቸውን ለማበርከት ዘወትር ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለራዕያቸው ስኬት የሚታትሩ፣ ተልዕኮአቸውን በልኩ ለመወጣት የሚጥሩ ተቋማት ማህበረሰብን በወጉ ለማገልገል አይቸገሩም፡፡ በሚሰጡት አገልግሎት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚፈጥሩት እርካታ ማህበረሰቡ በመንግስት ላይ ያለው እምነትም እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ መሰል ተቋማት መበራከት የመንግስትን አጠቃላይ አሰራር የተስተካከለ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ያለበት አጠቃላይ ቁመና ጥሩ ሲሆን ዘርፉ ለሚጠይቀው ሰፊና ዘርፈ ብዙ ተግባራት የበለጠ ራሱን ማዘጋጀትና ለላቀ ውጤት መስራት ግድ ይለዋል፡፡

ይህ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂም አጠቃላይ ሁኔታንና ሪፎርሙ ለመተግበር ያሉ ተቋማዊ፣ ሀገራዊና ዓለማዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ እየተነተነ በአህዝቦት ስራ ማጀብና በልኩ ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 5. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች ያላቸው ወሳኝ ሚና

ተቋማትን ከማህበረሰቡ ጋር ድልድይ ሆኖ በማገናኘት ረገድ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ ተቋማት ራዕያቸውን ፣ ተልኳቸውን፣ ግባቸውን በአግባቡ በማስተዋወቅ ከህብረተሰቡ ጋር አራሳቸውን የሚያገናኙት በህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች ነው፡፡ በተጨማሪም ተቋማት ከህብረተሰቡ የሚነሱ ፍላጎቶችንና ጥያቄዎችን ለይተው እንዲያውቁና ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ እና የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ መረጃዎችን በግልፅ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የህዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ሥራዎች ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

ተቋማችን የመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርምን ከመተግበር አኳያ በለውጥ ሂደት ውስጥ እያለፈ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን የለውጡን አስፈላጊነት የተቋሙ ሰራተኞች እና ተገልጋይ ህብረተሰብ ተገንዝበው ሪፎርሙን ስኬታማ ለማድረግ የህዝብና የኮሙኒኬሽን ግንኙነት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም የህዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ስራዎች ሪፎርሙን በተመለከተ ግንዛቤን በማሳደግ፤ አዎንታዊ እና አሉታዊ እሳቤዎችን በተገቢው መልኩ በማስተላለፍ፣ ግልፅነትን በመፍጠር እና ስኬቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

## 6. ባለድርሻ አካላት

### 6.1. ውስጣዊ ባለድርሻ አካላት

በፌደራል ቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ኢንሲቲትዩት ስር የሚገኙ ሰራተኞች የመንግስት አገልግሎትና አስተዳር ማሻሻያ ሪፎርም በቀጥታ የሚመለከታቸው ስለሆኑ ጉዳዩን ተገንዝበው ለስኬታማነቱ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 6.2. ውጫዊ ባለድርሻ አካላት

#### 6.2.1. ተገልጋዮች

- ተግባራዊ የሚደረገው የመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ቀልጣፋ እና ውጤታማ ሲሆን የመጨረሻው ተጠቃሚ ተገልጋዩ ነው፡፡ ስለሆነም የአጭር ግዜና እና የረዥም ግዜ ሰልጣኞች፣ ቴክኖሎጂ አልሚዎች የሪፎርሙን ዓላማ በአግባቡ እንዲገነዘቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

#### 6.2.2. ሌሎች ባለድርሻ አካላት

- በተቋማችን መዋቅር ገብቶ ለመስራት ፍላጎት ያላቸው ሥራ ፈላጊዎች እና ወደ ዘርፉ ለሚቀላቀሉ አዳዲስ ሠራተኞች ሪፎርሙን አስመልክቶ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
- አጋር አካላት በሪፎርሙ ትግበራ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ለስኬቱ የበኩላቸውን እንዲወጡ ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

#### 6.2.3. የመገናኛ ብዙሃን

- ሪፎርሙን በተመለከተ ለሚመለከታቸዉ የህብረተሰብ ክፍል መረጃውን ተደራሽ ለማድረግ ከመገናኛ ብዙሀን ጋር ተቀራርቦ መስራት ያስፈልጋል፡፡

#### 6.2.4. የሠራተኛ ማህበር አደረጃጀት

- ሪፎርሙ ለሠራተኛው፣ ለህብረተሰቡ እና ለሀገር ያለውን ፋይዳ አስመልክቶ ለሠራተኛ ማህበራት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 7. ቁልፍ መልዕክቶች እና የኮሙኒኬሽን ቻናል

ሪፎርሙ በሚፈለገዉ መልኩ ግቡን እንዲመታ አዳዲስ፣ ለየት ያሉ እና ውጤታማ ቁልፍ መልዕክቶችን በየጊዜዉ እየቀረጹ ለተቋሙ ሰራተኞች እና ለባለድርሻ አካላት ማስተላለፍ ወሳኝ ስራ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለዚህም የፖሊሲ ማሻሻያ ኮሚቴው በተቋሙ የሚተገበረውን የለውጥ ስርዓት አዳማጮችን/ተመልካቾችን ባገናዘበ ሁኔታ መልክቶችን ማዘጋጀ፤ አግባብነት ባለውን ቻናል መተላለፋቸውንም ማረጋገጥ እናም ውጤቱንም መከታተል ይጠበቅበታል፡፡

### 7.1. ቁልፍ መልዕክቶች

በተቋማችን የሚተገበረውን ሪፎርም በተመለከተ የሚታለለፉት ቁልፍ መልክቶች ይዘትም ከዘመናዊ አገልግሎት አሰጣጥ፤ ነጻና ገለልተኛ የሲቪል ሰርቪስ ከመገንባት፤ብዝኃነትና አካታችነትን ከማምጣት፤የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት ከማረጋገጥ፤ የዲጅታል ሲቪል ሰርቪስ ከመግንባት፤የሲቪል ሰርቪስ ገቢር ነቢብ አመራርና ተቋም ግንባታ እና የሥራ ምዘና እና የክፍያ ሥርዓት ከመገንባት አንጻር መሆን እንዳለባቸው ተለይተዋል፡፡

#### 7.1.1. የዘመነ አገልግሎት

የዘመነ አገልግሎት ማለት ተቋሙ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ለተጠቃሚ ምቹ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎችን በመተግበር የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መለዋወጥ ተከትሎ የሚነሱ ጥያቄዎችን መመለስ መቻል ማለት ነው።

ዋና ዋና መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡–

- በተቋማችን የተጠቃሚዎችን ተለዋዋጭ ፍላጎቶች መመለስ የሚያስችል የዘመነና ቅልጥፍናን የተላበሰ አገልግሎት መስጠት መርህ አድርጎ መስራት ይጠበቃል፡፡
    - ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የዘመናዊነት መገለጫ ነው
    - ተገልጋይ ተኮር አገልግሎት መስጠት የስራችን መርህ ነው
- ተሞክሮዎችን በመቀመር የአሰራር ሂደቶችን ማቀላጠፍ እና ተገልጋዮች ወቅቱን የጠበቀ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ ዘመኑ የሚጠይቀውን አገልግሎት መስጠት ወሳኝ ነው፡፡
    - ጥራት ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለተገልጋዮች እርካታ
    - ፍጥነትና ቀልጣፋነት የአገልግሎታችን ውበት

### 7.1.2. ነጻና ገለልተኛ የሲቪል ሰርቪስ መገንባት

ነፃና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ መገንባት ማለት ለፖለቲካ ያልወገነ ለሙያው ክብር ያለው፣ ገለልተኛና ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ መገንባት ማለት ነው፡፡

ዋና ዋና መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የዜጎች እርካታ ሊረጋገጥ የሚችለው በየትኛውም ፖለቲካዊ አመለካከት ተፅዕኖ ሥር ያልወደቀ፣ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በእኩል የሚያገለግል፣ የተሰጠውን ኃላፊነት በላቀ ሙያዊ ብቃት መወጣት የሚችል ሲቪል ሰርቪስ መገንባት ሲቻል ነው፡፡
    - በፍትሀዊ አገልግሎት ተገልጋዮችን ማርካት
    - ሙያዊ ብቃት ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት
    - ህዝባዊነት ለፍትሀዊ አገልግሎት
    - ከወገንተኝነት የፀዳ አገልግሎት የተገልጋዮችን እርካታ እናረጋግጥ
    - ለዜጎች ሀገራዊ ኩራት ከአድሎ የነጻ አገልግሎት

### 7.1.3. ብዝኃነትና አካታችነትን ያረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ ግንባታን ማረጋገጥ

ብሔርን፣ እድሜን፣ ጾታን፣ አካል ጉዳተኝነትን አካታች የሆነ እና የሁሉንም ተሳትፎ የሚያረጋግጥ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓት መገንባት ማለት ነው፡፡

ዋና ዋና መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ብሄር፣ እድሜ፣ ጾታን እና አካል ጉዳተኝነትን ያማከለ ሲቪል ሰርቪስ ግንባታን ማረጋገጥ የህልውናችን መሰረት ነው፡፡

- ○ አካታችነታችን ለህልውናችን
- ○ ብዝሀነት ለዘመነ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት

- ሁሉም ሰራተኛ የሚደመጥበት፤ የሚከበርበት እና ችሎታውን የሚገልጽበት የስራ አካባቢ በመፍጠር የላቀ ውጤታማነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
  - ○ ምቹ የስራ ከባቢ ለላቀ ውጤታማነት

### 7.1.4. የሥራ ምዘና እና የክፍያ ሥርዓት መገንባት

የሠራተኞችን ብቃት በአግባቡ በመመዘን፣ የምዝና ውጤታቸውን መሰረት ያደረገ የክፍያ ስርዓትን እውን የሚያደርግ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓት መገንባት ማለት ነው፡፡

ዋና ዋና መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የመንግስት አደረጃጀትና አወቃቀር የሚመራበትን ስታንዳርድ በመተግበር በምዘና ላይ የተመሰረተና የሰራተኛ ብቃትን መሰረት ያደረገ የክፍያና ጥቅማ ጥቅም ሥርዓትን በመተግበር የተወዳዳሪነትን መንፈስ በማስፈን የሲቪል ሰርቪሱን ውጤታማነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
  - ○ የዘመነ አደረጃጀት ብቃት ላለው ሲቪል ሰርቫንት
  - ○ የምዘና ጥራት ለተወዳዳሪነት
  - ○ ብቃት ለፍትሀዊ የክፍያ ስርዓት

### 7.1.5. የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት ማረጋገጥ፡

የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት ማረጋገጥ ማለት ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን በብቃት ለመወጣትና ህዝብን ለማገልገል አስፈላጊውን ክህሎት፣ እውቀት እና አመለካከት የታጠቁ አቅም ያላቸው የመንግስት ሰራተኞች መገንባት ማለት ነው።

ዋና ዋና መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡-

- የሠራተኞች ብቃትና ተወዳዳሪነት ለተቋማት ስኬታማነት ጉልህ አበርክቶ ይኖራቸዋል፡፡
  - ○ ብቃትና ተወዳዳሪነት ለተቋማዊ ስኬት
- የተለያዩ የስልጠና አማራጮችን በማመቻቸት የዜጎችን ብቃት በማጎልበት፣ ከሚጠበቅባቸው ኃላፊነት አንጻር የሚመዘኑበትና የሚመደቡበትን ሥርዓት ዕውን ማድረግ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡
  - ○ የጎለበተ የዜጎች ብቃት ለሰለጠነ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓት

### 7.1.6. የዲጅታል ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ

ዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ ማለት የመንግስት ተግባራትን ለማዘመን፣ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፣ የዜጎችን ተሳትፎ ለማሳደግ እና ፈጠራን ለማጎልበት ቴክኖሎጂን መጠቀም ማለት ነው። ይህም የሲቪል ሰርቪስ ስርዓቱን የበለጠ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና የህዝብን ፍላጎት ያገናዘበ አገልግሎት እንዲሰጥ ያስችለዋል።

ዋና ዋና መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡-

- በቴክኖሎጅ የታገዘ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት ተገልጋዮችን ማርካት ተቀዳሚ የዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ መርህ ነው፡፡
    - ተገልጋዮችን ለማርካት የዲጂታል አገልግሎት
    - ዲጂታላይዜሽን ለሲቪል ሰርቪስ ግንባታችን
    - ወቅቱን የዋጀ የዲጂታል ስርዓት ለተቀላጠፈ አገልግሎት
- ዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ የመንግስት ተግባራትን በማዘመን፣ አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ የዜጎችን ተሳትፎ በማሳደግ እና ፈጠራን ለማጎልበት የሚረዱ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ለህዝብ ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ አገልግሎት መስጠት ላይ ያተኮረ ነው።
    - የዲጂታል ስርዓት ለላቀ የዜጎች ተሳታፊነት
    - ፈጠራን ለማጎልበት የዲጂታል ሰርቪስ አገልግሎት

### 7.1.7. የሲቪል ሰርቪስ ገቢር ነቢብ አመራርና ተቋም ግንባታ

የሲቪል ሰርቪስ ገቢር ነቢብ አመራርና ተቋም ግንባታ ማለት ዓለማችን በፈጣን የለውጥ ሂደት ውስጥ የምትገኝ ከመሆኗ የተነሳ ያልተረጋጋ፣ የማይገመት፣ ውስብስብ እና የተምታታ ሁኔታ ውሰጥ መሆኗን በመገንዘብ የመንግሰትን የአስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርሙን አላማ ዳር ለማድረስ  የሚያስችሉ ተጨባጭ ግብዓቶችን እና ዘዴዎችን፣ ተጠቅሞ ውጤት ሊያመጣ የሚችል የአመራር እና የአሰራር ስርዓትን መገንባት ማለት ነው፡፡

- የሲቪል ሰርቪስ ገቢር ነቢብ አመራር ዋነኛ ትኩረት እንደ ሀገር የትናንትን ዕዳ፣ የዛሬን ነባራዊ ሁኔታና የነገን መፃኢ ዕድል በውል በመረዳት፣ በአግባቡ በመተንተን፣ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን አስቀድሞ በማስቀመጥ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓቱን ውጤታማ የሚያደርጉ አመራሮችን በስፋት ለማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡
    - ገቢር ነበብነት ውጤታማ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት
    - ገቢር ነበብ አመራርነት ለተሟላ ሀገራዊ እውቀት
    - ሁሉም ሰሪ እንደ መሪ

## 7.2. የምንጠቀማቸው የኮሙኒኬሽን ቻናል

- ለውስጥ ግንኙነት
    - የገጽ ለገጽ መድረክ
    - የማህበራዊ ትስስር ገጾች
    - ቪዲዮ ኮንፈረንስ
    - አስተማሪ ቪዲዮ
    - በራሪ ጽሁፎች
- ለውጪ ግንኙነት
    - ጋዜጣዊ መግለጫ

- ጋዜጣዊ ጉባኤ
- የኢንስቲትዩቱ የማህበራዊ ትስስር ገጾች

## 8. የአደጋ ጊዜ ግንኙነት

በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ተግባራት ውስጥ የአደጋ ጊዜ ወይም ቀውስ ኮሙኒኬሽን የሚያመለክተው በለውጥ ትግበራ ወቅት ያልተጠበቁ ክስተቶች ወይም ተግዳሮቶች ሲያጋጥሙ እነሱን ለመፍታት የሚደረግ የኮሚኒኬሽን ስልትን ነው። ያልተጠበቁ ክስተቶች ወይም ተግዳሮቶች በተፈጠሩ ጊዜ መረጃን በብቃት በማስተዳደር፣ አደጋዎችን በመቀነስ፣ ከተቋሙ ሰራተኞች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መተማመንን በማሳደግ ላይ ያተኮረ የግንኙነት አይነት ነው። በመሆኑም እየተተገበረ ያለው የመንግስት የአገልግሎት አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወን እንዲቻል ተገቢ የሆነ የአደጋ ጊዜ ግንኙነት ስልቶችን፣ ስትራቴጂዎችና ቴክኒኮችን ቀይሶ መስራት ይጠይቃል፡ ፡

እነዚህን ለውጤታማ ግንኙነት፣ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት፣ ግልጸኝነትን ለመፍጠር እና ምላሽ ሰጪነትን ለማሳየት፣ እምነትን ለመገንባት እና ለማቆየት ብሎም የተሳሳተ መረጃ እንዳይሰራጭ ለመከላከል ይረዳል።

በአደጋ ጊዜ ግንኙነት/ኮሚኒኬሽን የሚደረጉ ቁልፍ ተግባራት፡-

- ግልጽ የመገናኛ መስመሮችን መፍጠርና ማስተዋወቅ
- ተገልጋዩ በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ቋንቋን መጠቀም
- ለጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት
- የተዛቡ መረጃዎችን በወቅቱ ማረም
- የግብረ መልስ ስርዓት መዘርጋት

## 9. የሚጠበቁ ውጤቶች

የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የመንግስት አገልግሎት አስተዳዳር ማሻሻያ ሪፎርም ስራ በሶስት የተለያዩ ምዕራፎች ማለትም በዝግጅት፣ በትግበራ እና በማጽናት ምዕራፍ የሚከናወን ሲሆን፤ በዚህም መሰረት ይህ የኮሙንኬሽን ስትራቴጅ ሲተገበር የሚከተሉት ዋና ዋና ውጤቶች ይጠበቃሉ፡፡

- ሁሉም የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም ሰራተኞች፤ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት ስለ የመንግስት አገልግሎት አስተዳዳር ማሻሻያ ሪፎርም በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
- ሁሉም የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም ሰራተኞች፤ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት የመንግስት አገልግሎት አስተዳዳር ማሻሻያ ሪፎርምን ተግባራዊ ለማድረግ የራሳቸውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡
- ሁሉም የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም ሰራተኞች፤ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት ስለ የመንግስት አገልግሎት አስተዳዳር ማሻሻያ ሪፎርም ዙሪያ የግልጽነት ችግር ሲኖር ማብራሪያ ይጠይቃሉ፡ ፡

- ሁሉም የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም ሰራተኞች፤ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት በመንግስት አገልግሎት አስተዳዳር ማሻሻያ ሪፎርም የሚመጣውን የለውጥ አሰራር ተቀብለው ይተገብራሉ፡ ፡
- ሁሉም የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም ሰራተኞች፤ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት ስለመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ለውጥ የዳበረ አዎንታዊ አስተሳሰብ መኖር፡፡
- በመንግስት አገልግሎት አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ምክንያት የተገኙ አዎንታዊ ለውጦችና የተተገበሩ መልካም ተሞክሮዎች፡፡

## 10. የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ስልቶች፤

በተቋሙ ታቅዶ ለውጥ ለማምጣት እየተተገበረ ያለውን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ለማስፈጸም የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ ስልቶች አስፈላጊ ናቸው፡፡ከዚህ በመቀጠል እነዚህ ማስፈጸሚያ ስልቶች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

- ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የሚመጡ ሪፎርም ተኮር አቅጣጫዎችን ለሥራ መመሪያነት መጠቀም፣
- የተቋማችን የውስጥም የውጪም ባለድርሻ አካላትን ማዕከል ያደረጉ መልዕክቶችን በተለያየ መልዕክት ማስተላለፊ መንገዶች አመቺ እንዲሆን አድርጎ መቅረፅና ማሰራጨት፣
- በየደረጃው ካሉ አካላት ጋር ሪፎርሙን ሊያሳካ የሚችል ግልጽ የሆነ የአሰራር ግንኙነት መዘርጋት፣
- ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት የተግባቦት ስልት መከተል (ወቅታዊ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ፣ የሚያጋጥሙ ስጋቶችን መቅረፍ)፣
- ሰራተኛው በየደረጃው ሪፎርሙን ለማሳካት የሚያደርገውን የነቃ ተሳትፎ ማበረታታት፣
- የተለያዩ መረጃን ለማስተላለፍ የሚረዱ የኮሙኒኬሽን ቻናሎችን እንደ አመቺነታቸው መጠቀም፣

## 11. የክትትልና የግምገማ ስርዓት፤

በተቋማችን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም የአተገባበር ስርዓትን በሚጠበቀው አግባብ ለማከናወንና ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ በጠንካራ ተነሳሽነትና ባለቤትነት መንፈስ ይዞ ግልፅነትና ተጠያቂነትን በተላበሰ መንገድ መፈፀም ይገባል፡፡ በመሆኑም

- የኮሙኒኬሽን ሥራዎችን ውጤታማነት ለመለካት የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ዕቅድና መረሀ–ግብር ማዘጋጀት፣
- የሪፎርም ትግበራውን ለመከታተል የሚያስችል የውጤት አመላካቾችን መቅረጽ (KPIs)፣
- የትኩረት ቡድን ውይይት በማካሄድ ስለ ሪፎርም አፈጻጸም መረጃዎችን ማሰባሰብ፣
- የተሰባሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ትንታኔ መስራትና ውጤቱን ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ማሳወቅ፣
- የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂውን መከለስ፣

## 12. ማጠቃለያ

አሁን ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ ዜጎች በተለያየ አማራጭ የሙያ ስልጠናን አግኝተው በእውቀት፣ በክህሎትና በስራ ስነ ምግባር ታንጸው በራሳቸው የሚተማመኑ አምራች ኃይል ከመሆን አልፈው ምቹ የስራ እድል ለመፍጠር፣ ሰላምንና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ብሎም ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ሀገር እና ዓለምን ለመገንባት ትልቅ አበርክቶ እንዲኖራቸው ያለመና ትልቅ ራዕይን ያነገበ ነው፡፡

በኢንስቲትዩታችን ተግባራዊ ለማድረግ እየተከናወነ ያለው የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ሥራዎች የተቋሙን አገልግሎት ቀልጣፋና የዘመነ ከማድረግ አንፃር መሰረታዊ ለውጥን እንደሚያስገኝ የሚጠበቅ ሲሆን ዋነኛ ተልዕኮውን ለማሳካት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ይታመናል፡፡

ይህንን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ውጤታማ ለማድረግ  የኮሙዩኒኬሽን ስልታችን ለዜጎችና ሰራተኞች መረጃዎች በተለያዩ አማራጮች ጊዜውን በጠበቀ በተሟላና ግልጽ በሆነ መንገድ ተደራሽ መሆናቸውንና በቂ ግንዛቤ መፈጠሩን ቅድሚያ ሰጥቶ በማረጋገጥ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር መስተጋብራዊ መድረኮችን በማዘጋጀትና እና ንቁ ተሳትፎዎች እንዲኖሩ በማድረግ፣ ስጋቶችና ተግዳሮቶችን በጥንቃቄ በመቋቋምና በመቀነስ፣ ተከታታይ የሆነ የድጋፍ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት፣ ወቅታዊ ግብረ መልስ በመስጠት፣ ለስኬቶቻችን ትርጉም በመስጠትና በማክበር  የሪፎርሙን ዓላማዎች ለማስረጽ አልሞ መስራትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡
፡

በዚህ መሰረት ይህ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ በየደረጃው ቁልፍ መልዕክቶችን በመቅረጽና በማስተላለፍ፣  በውጤታማ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ የተሻሻለ ተቋማዊ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አጽንኦት በመስጠት እንከን የለሽ ሽግግር እንዲኖርና ቀጣይነት ያለው ተፅእኖን ማረጋገጥ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ በማተኮር ጥሩ ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን የበለጠ ምላሽ ሰጪ የሆነና ተገልጋዩን/ዜጎችን ያማከለ የሲቪል ሰርቪስ ስርዓት በኢንስቲትዩቱ እንዲፈጠር ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ይጠበቃል።

## 13. የድርጊት መርሀ ግብር

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈጻሚ አካል | የከንውን ወቅት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢንስቲትዩቱን የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ማስተግበሪያ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት | በሰነድ | 01 | በቡድን አባላት | ሰኔ 25/2016 ዓ.ም | |
| 2 | የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርምን አስመልክቶ ቁልፍ መልዕክቶችን መቅረጽና በተለያየ ኮሙኒኬሽን ቻናል ማስተላለፍ | | | | | |
| 2.1 | የዘመነ አገልግሎት | በቁጥር | 04 | በቡድን አባላት | | |
| 2.2 | ነጻና ገለልተኛ የሲቪል ሰርቪስ መገንባት | በቁጥር | 05 | በቡድን አባላት | | |
| 2.3 | ብዝኃነትና አካታችነትን ያረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ ግንባታን ማረጋገጥ | በቁጥር | 03 | በቡድን አባላት | | |
| 2.4 | የሥራ ምዘና እና የክፍያ ሥርዓት መገንባት | በቁጥር | 03 | በቡድን አባላት | | |
| 2.5 | የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት ማረጋገጥ፡ | በቁጥር | 02 | በቡድን አባላት | | |
| 2.6 | የዲጅታል ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ | በቁጥር | 05 | በቡድን አባላት | | |
| 2.7 | የሲቪል ሰርቪስ ገቢር ነቢብ አመራርና ተቋም ግንባታ | በቁጥር | 03 | በቡድን አባላት | | |
| 3 | ቁልፍ መልዕክቶችን በዲጂታላይዜሽን በማዘጋጀት ግንዛቤን መፍጠርና ሰራተኞችን ዝግጁ ማድረግ | በቁጥር | 07 | በቡድን አባላት | | |
| 4 | ቁልፍ መልዕክቶችን መነሻ ያደረገ የፓናል ውይይት ማድረግ | በቁጥር | 06 | በቡድን አባላት<br>በተቋም አመራሮች | | |
| 5 | የውይይቱን ጭብጥ ለማስረጽ የሚረዱ ግብረ መልሶችን መስጠት | በቁጥር | 06 | በቡድን አባላት | | |
| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈጻሚ አካል | የከንውን ወቅት | ምርመራ |
| 5 | የተለያዩ የኮሙኒኬሽን ቻነሎችን በመጠቀም የሪፎርም ትግበራ ሂደቱን በየደረጃው ማስተዋወቅ | | | | | |
| 5.1 | የዝግጅት ምዕራፍ | | 02 | በቡድን አባላት | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.2 | የትግበራ ምዕራፍ | | 04 | በቡድን አባላት | | |
| 5.3 | የማጽናት ምዕራፍ | | 03 | በቡድን አባላት | | |
| 6 | የሪፎርም ትግበራ ሂደቱን በየደረጃው ለሚመለከተው አካል በሪፖርት ማሳወቅ | በቁጥር | 12 | በቡድን አባላት | | |